## የፍትህ ሚኒስቴር

# የመብቶች መግለጫ

በቁጥጥር ሰው ለዋለ የሚሰጥ
ከ 16 አመት በላይ የሆኑ ታዳጊዎች፤ የአዋቂ ግብረ አበር ወይም ተባባሪ የሆኑ በፈረንሳይ የወንጅል ህግ አንቀጽ 706-73 ስር ጥፋት የፈጸሙ

**ይህ መረጃ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ሊሰጦት ይገባል።**
**ከእርስዎ ፍላጎት ጋር የማይቃረን ከሆነና የህግ ሂደቱ ላይ ተፅዕኖ የማያሳድር ከሆነ የወላጅነት ኃላፊነት የያዙ ሰዎች ተመሳሳይ መረጃ ይሰጣቸዋል።**
**በህግ ጥላ ስር በሚቆዩበት ግዜ ሁሉ ይህ ዶክመንት ከእርስዎ ጋር ሊቆይ ይችላል።**

በህግ ጥላ ስር የሚገኙት በተደራጀ ወንጀል እና አነስተኛ ወንጀል ስር የአዋቂ ግብረ አበር ወይም ተባባሪ ሆነው በእስር ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ፈፅመዋል ወይም ለመፈፀም ሞክረዋል የሚል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጥርጣሬዎች በመኖራቸው ምክንያት መሆኑ ተነግሮዎታል።

ፈፅመዋል ተብለው ስለተጠረጠሩበት ወንጀል አይነት፣ ስለተፈጸመበት ቦታ እና ግዜ፣ እንዲሁም በቁጥጥር ስለዋሉበት ምክንያት የማወቅ መብት አሎት።

ስለነዚህ ነገሮች እስከ 24 ሰዓታት ሊቆይ በሚችለው በቁጥጥር ባሉበት ግዜ ውስጥ ይነገርዎታል።

ይህ ግዜ ሲያልቅ አቃቤ ህግ (ወይም ጉዳዩን የሚያየው ዳኛ ወይም የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) በቁጥጥር ስር የሚውሉበትን ግዜ ለተጨማሪ 24 ሰዓታት ሊያራዝሙው ይችላል። እንደ አስፈላጊነቱ በቪዲዮ ኮንፍረንስም ቢሆን ወደዚህ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ።

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና የምርመራ ሂደቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው፤ እያንዳንዳቸው 24 ሰዓታት የሚሆኑ ሁለት ተጨማሪ ማራዘሚያዎች በነጻነት እና እስር ዳኛ አልያም ጉዳዩን በሚመለከተው ዳኛ ሊሰጡ ይችላሉ።

ነገር ግን የመጀመሪያው 48 ሰዐት ሲያልቅ የሚከተሉት የምርመራ ሂደቶች ተገቢ ሆነው ከተገኙ፤ የነጻነት እና እስር ዳኛው በአቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ዳኛ ጥያቄ መሰረት እስሩ አንዴ ብቻ እና ለ 48 ስዓታት እንዲራዘም ሊወስን ይችላል።

በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ ሲጠናቀቅ በአቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩን በሚመለከተው ዳኛ ውሳኔ መሰረት ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ወይም ሊለቀቁ ይችላሉ። በመጀመሪያው ሁኔታ፤ ፍርድ ቤት የሚቀርቡት በተመሳሳይ ቀን ይሆናል። በግዛቱ ለዚሁ የሚሆኑ ቦታዎች ካሉ እና እስርዎ 72 ሰዐታት ካላለፈ፤ እስርዎ ካበቃበት አንስቶ 20 ሰዓታት በማይበልጥ ግዜ ውስጥ በሚቀጥለው ቀን ሊቀርቡ ይችላሉ። እስርዎ 72 ሰዓታት ካለፈ፤ ፍርድ ቤት የሚቀርቡት እስርዎ በሚያበቃበት ቀን ይሆናል።

## በተጨማሪም፤ የሚከተሉት መብቶች እንዳሎት ተነግሮዎታል፡-

**ለተወሰኑ ሰዎች ስለሁኔታው ማሳወቅ**

ወላጆችዎ ወይም ሞግዚትዎ ወይም በአድራነት የሚመለከትዎት ግለሰብ ወይም ድርጅት የታሰሩበትን ሁኔታ፣ ምክንያት፣ ግዜ እና ቦታ እንዲሁም ስለተጠረጠሩበት ወንጀል ሁኔታ እንዲያውቁ ይደረጋል።

አብሮት ለሚኖር ሰው፣ ወይምከወላጅዎ ለአንዳቸው፣ወይምከወንድሞችዎወይምእህቶችዎ አልያም ከሞግዚትዎ ለአንዳቸው በህግ ጥላ ስር ስላሉበት ሁኔታ በስልክ ማሳወቅ ይችላሉ።

ቀጣሪዎንም ማሳወቅ ይችላሉ።

የውጭ ዜጋ ከሆኑ፤ ለሀገርዎ ቆንጽላ ኃላፊዎች ማሳወቅ ይችላሉ።

ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ካልኖሩ በስተቀር እነዚህ ጥያቄዎችዎ ባነስዋቸው ከ 3 ሰዓት በማይበልጥ ግዜ ውስጥ ይስተናገዳሉ።

ሆኖም ግን የማሳወቁ ሂደት መረጃን በመሰብሰብ ወይም በሰው ህይወት፣ ነፃነት ላይ አደጋን የሚፈጥር ከሆነ አቃቤ ህግ (ወይም ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ወይም የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) ሊያዘገየው ወይም ሊያግደው ይችላል። ህጋዊ ተወካይዎን የማሳወቁ ሂደት እስርዎ ከተራዘመ ከ 24 ሰዐት በላይ፤ ካልተራዘመ ደግሞ ከ አስራ ሁለት ሰዐት በላይ ሊራዘም አይችልም።

እስርዎ ከ 48 ሰዓታት በላይ ከተራዘመ፤ በተመሳሳይ ምክንያት እስሩ መራዘሙን ለቤተሰብዎ ወይም ቀጣሪዎ የማሳወቁ ሂደት በነጻነት እና እስር ዳኛ (ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ዳኛ) ሊራዘም ይችላል።

## ከግለሰብ ጋር ስለመገናኘት

በህግ ቁጥጥር ስር እርስዎ እንደዋሉ ከተነገራቸው ሰዎች ከአንዳቸው ጋር በጽሁፍ፣ ስልክ ወይም ፊት ለፊት ለመገናኘት መጠየቅ ይችላሉ።

ጥያቄዎ በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ምክንያት ጋር አብሮ የማይሄድ ከሆነ፤ ወይም ወንጀል እንዲፈጸም መንገድ የሚከፍት ከሆነ መርማሪ ኦፊሰሩ ጥያቄዎን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። የተጠቀሰው ኦፊሰር ወይም እሱ የሚሾመው ግለሰብ የሚያደርጉት ግንኙነት በእርሱ ቁጥጥር ስር፤ እንዲሁም በምን አይነት ሁኔታ እና ለምን

ያህል ግዜ ከ 30 ደቂቃ በማይበልጥ መደረግ እንዳለበት ይወስናል።

የእስር ግዜዎ ከ 48 በላይ ከተራዘመ፤ መርማሪ ኦፊሰሩ ከቆንጽላ ኃላፊዎች ጋር የመገናኘት ጥያቄዎን ሊከለክል አይችልም።

## በዶክተር ስለመመርመር

በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ግዜ አንስቶ እስሩም በሚራዘምበት ግዜ በዶክተር ለመመርመር ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። የእስር ግዜዎ ከ 48 ሰዓት ካለፈ፤ በዶክተር የመመርመር ግዴታ ያለብዎት ሲሆን አዲስ የህክምና ምርመራ የመጠየቅ መብት እንዳሎትም ይነገሮታል። እነዚህ ጥያቄዎች በወላጆችዎ፣ ሞግዚትዎ ወይም በአደራ በያዝዎት ግለሰብ ወይም ተቋም ሊቀርቡ ይችላሉ።

የህክምና ምርመራ እንዲደረግልዎት ጠበቃዎ ሊጠይቅ ይችላል።

## ቃል መስጠት፣ ጥያቄ መመለስ ወይም ዝም ማለት

ማንነትዎን ካረጋገጡ በኋላ፤ ክስዎ በሚካሄድበት ግዜ የሚከተሉት መብቶች አሎት፦

- ቃል መስጠት
- ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ መስጠት
- ወይም ዝም ማለት

## ከህጋዊ ወኪልዎ ጋር ስለመቅረብ

ስልጣን ያለው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በክስ ሂደትዎም ሆነ በቃለ ምልልስ ወቅት የወላጅነት ስልጣን ካለው አካል ጋር አብረው ይቀርባሉ። አስፈላጊ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ከሚሾመው አዋቂ ሰው ጋር ወይም እርስዎ ከሚመርጡት ሌላ አዋቂ ጋር አብረው ሊቀርቡ ይችላሉ።

## የጠበቃ ድጋፍ ስለማግኘት

**የግድ በጠበቃ መደገፍ አለብዎት**

### የጠበቃ ምርጫ

በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ግዜ አንስቶ፣ በክስ ሂደትዎ ግዜ፣ እና በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ በተራዘመበት በማንኛውም ግዜ ከመረጡት ጠበቃ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። ጠበቃ መቅጠር ካልቻሉ ወይም የመረጡት ጠበቃ ሊገኝ የማይችል ከሆነ አቃቤ ህጉ (ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ወይም የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) ወዲያውኑ ጠበቃ ተመድቦ እንዲያግዝዎ መጠየቅ ይችላሉ።

ጠበቃዎ በወላጆችዎ<u>ወይም</u>፣ በሞግዚትዎ <u>ወይም</u>ወይም አደራ በተሰጠው ድርጅት ሊሾምልዎ ይችላል።

### የህግ ድጋፍ እና የምላሽ ግዜ

የውይይቱን ምስጢራዊነት በጠበቀ መልኩ ጠበቃዎ ለ 30 ደቂቃ ሊያገኝዎ ይችላል። በቁጥጥር ስር የሚውሉበት ግዜ ከተራዘመ፤ ጠበቃዎን በድጋሜ ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ።

በእርስዎ ጥያቄ መሰረት ጠበቃዎ እርስዎ የሚሳተፉባቸውን የክስ ሂደቶች፣ክርክሮች፣ምልልሶች ወይም ማንነትን የመለያ ውይይቶች ላይ መሳተፍ ይችላል።

ይህ በሚሆንበት ግዜ፣ ማንነትዎን ለመለየት ከሚደረጉ ጥያቄ እና መልሶች ውጪ የመጀመሪያ ችሎትዎ ጠበቃዎ ስለ ችሎቱ ከተነገራቸው 2 ሰዓት እስከሚያልፍ ድረስ ጠበቃዎ ባሌሉበት ችሎት አይካሄድም። ነገር ግን የምርመራው ሁኔታ የሚያስገድድ ከሆነ በአቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩን በሚያየው ዳኛ ፍቃድ የክስ ሂደትዎ ጠበቃዎ ባሌለበት ወዲያውኑ ሊጀምር ይችላል።

ክስ ማንበብ ወይም ክርክር እየተካሄደ ባለበት ግዜ ጠበቃዎ ከደረሰ፤ ከጠበቃዎ ጋር ይነጋገሩ ዘንድ ሂደቱ እንዲቆምልዎት መጠየቅ ይችላሉ።

ነገር ግን አሳማኝ ምክንያቶች ከኖሩ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤ አቃቤ ህግ፣ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳኛ ወይም የነጻነት እና እስር ዳኛ ክስዎ በሚነበብበት ግዜ 12 ሰዓት ለማይበልጥ ግዜ የጠበቃዎን ድጋፍ እንዳያገኙ ማገድ ይችላል። የተጠረጠሩበት ወንጀል ከአምስት አመት በማያንስ እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ እገዳው ሊታደስ ይችላል።

## የትርጉም አገልግሎት ስለማግኘት

ፈረንሳይኛ የማይናገሩ ወይም የማይገባዎት ከሆነ ከክፍያ ነጻ በሆነ መልኩ በክስዎ ሂደትም ሆነ ከጠበቃዎ ጋር በሚነጋገሩበት ግዜ የትርጉም አገልግሎት የማግኘት መብት አሎት።

## እስር እንዲቋረጥልዎት ስለማመልከት

በእስር የሚቆዩበት ግዜ እንዲራዘም ሊወሰን ፍርድ ቤቱ በሚቀመጥበት ግዜ፤ ግዜው እንዳይራዘም አቃቤ ህጉን፣ ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ወይም የነጻነት እና እስር ዳኛ መጠየቅ ይችላሉ።

## ከጉዳይዎ ጋር የሚገናኙ የተወሰኑ ነገሮችን የማግኘት መብት

በእርስዎ ወይም በጠበቃዎ ጥያቄ መሰረት እና በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ ከመራዘሙ በፊት የሚከተሉትን መጠየቅ ይችላሉ፦

- በቁጥጥር ስር መዋልዎን የሚገልፅ መግለጫ
- የመረመርዎ ዶክተር የሰጠው የህክምና ሰርቲፊኬት.
- የክስ ሂደትዎ-ጉባኤ

## አቃቤ ህጉን ስለማናገር

በቁጥጥር ከዋሉበት ግዜ አንድ አመት በኋላ መቀበልዎን በሚያረጋግጥ ድብዳቤ ወይም መቀበልዎን ለመዝገብ ቤት በማሳወቅ የክስዎን ፋይል ለማየት አቃቤ ህጉን መጠየቅ ይችላሉ።

## የሚስጥራዊነት መብት

የቴክኒክ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የክስ ሂደትዎ በፊልም ይቀረጻል። እነዚህን ቅጂዎች እንዲያስተላልፍ ለማንም አይፈቀድም።

ቅጂዎቹ የሚታዩት በችሎት ግዜ ሲሆን የክስ ሂደቱን ቃለ ጉባኤም ሆነ እርስዎን ሊያስለይ የሚችል ምንም አይነት ነገር እንዲታተም አይፈቀድም።